# አይፋቅም

በዓለት ላይ ታንጾ በወርቅ የተጻፈ
በሰማያዊ ክብር ጸንቶ የገዘፈ
የማይገረሰስ ዘመን የማይሽረው
የዓለም ማዕበል የማይገፈትረው
ሊጥሉት፣ ሊፍቁት፣ ሊያጠፉት ቢጥሩ
የማይነቀንቁት ከጠበቀው ስሩ
የማይደበዝዝ ነው ደምቆ የሚያበራ
የአፍሪካ ፀሐይ፣ የነፃነት አውራ
የጥቁር ሕዝብ ሰንደቅ የድል ብርሃን ተስፋ
የማንነት መብራት መቼም የማይጠፋ . . .
"ኢትዮጵያ" ስሟ ነው "ኢትዮጵያ" ዓርማችን
ሲያበራ የሚኖር መሪ ኮከባችን።
"ኢትዮጵያ" ስሟ ነው አይጠፋም፣ አይወድቅም
ቀደምት፣ ባለታሪክ ክብሯ አይፋቅም
በመንፈሣዊውም በዓለማዊ መዝገብ
"ኢትዮጵያ" ስሟ ነው ቀድሞ የሚታሰብ።
ስሟን ሊሰርዙ፣ ስሟን ሊያቆሽሹ
ከማንነታቸው ተጣልተው የሸሹ
ይደክማሉ እንጂ ያልታደሉ ሆነው
"ኢትዮጵያ" ተተክሏል ምንም ሀይል ላይነቅለው።
በእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ታትሟል ቀለሟ
ኢትዮጵያ "ኢትዮጵያ" ናት ይዘመራል ስሟ . . .
ኢትዮጵያ "ኢትዮጵያ" ናት፤ ገና ይነግሣል ስሟ።

---

ቴዎድሮስ አበበ
Washington, DC
ጥቅምት ፳፰ ቀን ፳፻፲ ዓ.ም. | November 7, 2017